# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 348 ጥር 1 2007 ገጽ 1


ኢትዮጵያን በግፍና በዝርፊያ የሚገዛው የህወሀት ጉጅሌ በመንግስትነትና በወንበዴነት መሀል ያለውን ልዩነት ከ፳፫ ዓመት ስልጣን ዘመን ብኋላ እንኳን ሊገለጥለት አልቻለም። ወይም እንዳመችነቱ ሁለቱን እያምታታ መቀጠሉን እንደብልህነት ቆጥሮታል።

ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ሁላችንም አንዳርጋቸው ጽጌን እንሁን!!!

በህወሓት ሙሉ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የፌደራል ፓሊስ በእሁድ ታህሣሥ 28 ቀን 2007 ዓ.ም. የቴሌቪዥን ፕሮግራሙ በግፍ እስር ላይ የሚገኘውን የግንቦት 7 ዋና ፀሐፊን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አቅርቦት ነበር። ይህ የ10 ደቂቃዎች ምስል ለቁጥር በሚያታክት ብዛት ተቆራርጦ የተቀጣጠለ በመሆኑ አቶ አንዳርጋቸው ምን ተጠይቆ ምን እንደመለሰ ማወቅ አይቻልም። ስለሆነም በንግግሩ ይዘት ላይ አስተያየት መስጠት ይናገረው አይናገረው በአልታወቀ ጉዳይ ማብራሪያ መስጠት ይሆናል። ስለዚህም፣ በንግግሩ ይዘት ላይ ጊዜ ከማጥፋት ህወሓት አንዳርጋቸው ጽጌን አሁን ማቅረብ ለምን እንደፈለገ መተንተን ይበልጥ ጠቀሜታ አለው ብሎ ግንቦት 7 ያምናል።

አሁን ህወሓት በውስጥም በውጭም ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ የገባበት ጊዜ ነው፤ በራሱ በድርጅቱ ውስጥም ሰላም የለም። ህወሓት የትግራይ ክልል ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር እንደሆነ አድርጎ በመቁጠር መላዋን ኢትዮጵያን ለመዝረፍና ለማጥቃት እንደ መንደርደሪያ፤ በሌላኛው የኢትዮጵያ ክፍል ተቃውሞ ሲበዛበት ደግሞ እንደ መደበቂያ ዋሻ ሲጠቀምበት የነበረው ጊዜ አብቅቶ የትግራይ ሕዝብ በህወሓት ላይ ማመጹ በግልጽ በተግባር እየታየ ነው። በርካታ የትግራይ ልጆች በህወሓት ላይ ነፍጥ አንስተዋል፤ ከፊሎቹ ደግሞ በሰላማዊ ትግል ህወሓትን ማስወገድ ይቻላል ብለው በክልላቸውም ከክልላቸውም ውጭ ከህወሓት ጋር ፍልሚያ ገጥመዋል። ህወሓት መሠረቴ ነው ከሚለው የትግራይ ክልል ፈጽሞ ሊነቀል የሚችል መሆኑ ግልጽ ምልክቶች እየታዩ ነው። የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) ከትግራይና ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያገናኘው የአማርኛና የትግርኛ የቴሌቪዥን ፕሮግራም መጀመሩ የህወሓት ሹማምንትን ናላ ያዞረ እርምጃ ሆኗል።

የህወሓት ሌላው መተማመኛው የጦር ሠራዊቱ ነበር። ህወሓት፣ የኢትዮጵያን መከላከያ ጦር ሠራዊት ዘረኛ በሆነ መንገድ አደራጅቶ፤ ከፍተኛ አመራሩን በታማኝ አባላቱ ሞልቶ ተደላድሎ የተቀመጠ መስሎ ታይቶ ነበር። አሁን ግን ይህም ምስል አሳሳች እንደሆነ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት የኢትዮጵያ ጠላት የሆነውን ህወሓትን የማገልገል ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን፤ እንዲያውም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመቆም የህወሓትን ውድቀት ለማፋጠን ያላቸውን ጉጉት በግልጽ እያሳዩ ነው። አየር ኃይል ውስጥ ያለው ተቃውሞ ገሀድ የወጣ ዜና ሆኗል። እንደ አየር ኃይል ገሀድ የወጣ ዜና አይሁን እንጂ በሌሎችም የሠራዊቱ ክንፎች ያለው አመጽ ተመሳሳይ የጡዘት ደረጃ ላይ ደርሷል።

ብአዴን እና ኦህዴድ ውስጥ ለአገራቸው ለኢትዮጵያ፣ እንወክለዋለን ለሚሉት ሕዝብ እና ለራሳቸው ክብር ያላቸው አባላት ብቅ ብቅ እያሉ ነው። ብአዴንንና ኦህዴድ እንደ ድሮ ፍጽም ታማኝ አገልጋዮች የመሆናቸው ጊዜ እያበቃ ነው። ደኢህዴንም ቢሆን ሙሉ በሙሉ የሚታመን አይደለም። ጊዜው ለህወሓት እጅግ የመከፋቱ ምልክት ደግሞ እራሱ ህወሓት ውስጥም ስምምነት የሌለ መሆኑ ነው። ህወሓት ይይዘው ይጨብጠው ጠፍቶታል።

ለዓመታት የዘለቀው የሙስሊም ወገኖቻችን ተቃውሞ እረፍት ነስቶት እያለ በባህርዳር የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ወገኖቻችን ተቃውሞ ተጨመረበት። የአምቦውን ተቃውሞ አዳፈንኩ ሲል የጎንደር ተቀሰቀሰበት። ለጉራና ለሀብት ዘረፋ ሲል ያስጀመረው የአባይ ግድብ፣ ጥበቃው ብቻ እንኳን ፋታ የሚነሳ ሥራ ሆነበት። ጋምቤላ፣ አፋርና፣ ሶማሊ የግጭት ቀጠናዎች ከሆኑ ዓመታት አስቆጠሩ።

ከላይ የተዘረዘሩት ጉምጉምታዎች፣ ተቃውሞዎችና አመጾች ተቀናጅተው የመጡ ዕለት መድረሻ እንደሚያጣ የተገነዘበው ህወሓት ትኩረት ማስቀየሻ መፈለጉ ግድ ነበር። በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት በአሁኑ ሰዓት የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ወደ ሚዲያ መቅረብ ምክንያቱ ይህ ነው።

አንዳርጋቸውን ወደሚዲያ በማቅረብ ትኩረትን የማስቀየስ ስትራቴጂ!

.... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

ግዜ

## ኢትዮጵያዊያን አንዳርጋቸውን ሲያዩ የሚታያቸው ጽናት፣ አርበኝነትና አልበገር ባይነት ነው

*ግንቦት 7 "ሁላችንም አንዳርጋቸው ጽጌን እንሁን!!!" በሚል ርእስ ዛሬ ታህሳስ 29 ቀን ባሰነበበው ርእሰ-አንቀጽ፤* በህወሓት ሙሉ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የፌደራል ፖሊስ እሁድ እለት በቴሌቪዥን ፕሮግራሙ በግፍ እስር ላይ የሚገኘውን የግንቦት 7 ዋና ፀሐፊን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ለ 10 ደቂቃ አቅርቦት እንደነበር በማውሳት፤ይህ የ10 ደቂቃዎች ምስል ለቁጥር በሚያታክት ሁኔታ ተቆራርጦ የተቀጣጠለ በመሆኑና አቶ አንዳርጋቸው በትክክል ምን እንዳለ የሚያስረዳ ባለመሆኑ፤ በይዘቱ ላይ አስተያዬት መስጠት አስፈላጊ እንዳልሆነ ገልጿል።

ከዚያ ይልቅ ህወሀት አንዳርጋቸውን ለምን አሁን ሊያቀርበው ፈለገ?የሚለውን ነጠብ ማዬት እንደሚያስፈልግ የጠቆመው ግንቦት 7፤ ህወሀት በውስጥም፣ በውጪም በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ የገባበት ወቅት በመሆኑ በተለይ ውስጣዊ ውጥረቱን ለማስተንፈስና አቅጣጫ ለማስቀየር አንዳርጋቸውን በተቆተራረጠ ምስልና ድምጽ አጅቦ ማቅረቡን ጠቅሷል። "የህወሓት ሌላው መተማመኛው የጦር ሠራዊቱ ነበር።"ያለው ግንቦት 7፤ ህወሓት፣ የኢትዮጵያን መከላከያ ጦር ሠራዊት ዘረኛ በሆነ መንገድ አደራጅና ከፍተኛ አመራሩን በታማኝ አባላቱ ሞልቶ ተደላድሎ የተቀመጠ መስሎ ቢቆይም አሁን ግን የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት የኢትዮጵያ ጠላት የሆነውን ህወሓትን የማገልገል ፍላጎት እንደሌላቸውና ይልቁንም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመቆም የህወሓትን ውድቀት ለማፋጠን ያላቸውን ጉጉት በግልጽ እያሳዩ መሆናቸውን መረጃዎችን ዋቢ አድርጎ አብራርቷል።

እንደ አየር ኃይል ተቃውሞ ገሀድ የወጣ ዜና አይሁን እንጂ በሌሎችም የሠራዊቱ ክንፎች ያለው አመጽ ተመሳሳይ የጡዘት ደረጃ ላይ መድረሱን የገለጸው ግንቦት 7፤ብአዴን እና ኦህዴድ ውስጥም ለአገራቸው ለኢትዮጵያ እና እንወክለዋለን ለሚሉት ሕዝብ እና ለራሳቸው ክብር ያላቸው አባላት ብቅ ብቅ እያሉ ነው ብሏል። እነኚህንና ሌሎችንም በመላ ሀገሪቱ የተቀጣጠሉትን የመብት ጥያቄዎችና አመጾች የተነተነው ግንቦት 7፤ "ተቃውሞዎችና አመጾች ተቀናጅተው የመጡ ዕለት መድረሻ እንደሚያጣ የተገነዘበው ህወሓት ትኩረት ለማስቀየስ ሲል አቶ አንዳርጋቸውን እንዳቀረበው ገልጿል። ..... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ ለሦስተኛ ግዜ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን ለሶስተኛ ጊዜ በቴሌቪዥን ማቅረቡ ኢትዮጵያዉያንንነ አስቆጣ

ባሳለፍነው እሁድ የጉጅሌው ወያኔ ልሳን የሆነውና በኢትዮጵያውያን ዘንድ የአገዛዙ የውሸት ቋት በሚል መጠሪያ በሚታወቀው ቴሌቪዥን፤ በ June 23, 2014 እ.ኤ.አ ፍጹም አለማቀፍ ህግን በጣሰ ውንብድና ከየመን ሰንአ አየር ማረፊያ ታፍነው ለጉጅሌው ወያኔ ተላልፈው የተሰጡትንና በጠላት እጅ የወደቁትን የንቅናቄያችን ዋና ፀሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ለ3 ጊዜ እንደ ተለመደው በቆርጦ ቀጥል በተገጣጠመ ቪዲዮ ለእይታ ቀርበዋል። ላለፉት 6 ወራት በጨለማ ክፍል ተወርውርው ከፍተኛ ስቃይና ሰቆቃ እየተፈፀመባቸው፤ በጽናት ተቋቁመው ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈሉ የሚገኙት የንቅናቄያችን ዋና ፀሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አስመልክቶ የቀረበውን ከ 18 ጊዜ በላይ የተከታተፈና የተገጣጠመ የ 13 ደቂቃ ቪዲዮን በተመለከተ በውጭ እና በአገር ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን አስተያየትና ቁጣቸውን እየሰነዘሩ መቀጠላቸው የታወቀ ሲሆን ቪዲዮው ፋሺስቱ ወያኔ የገባበትን ኪሳራና ውጥረት ከማሳበቁም በላይ የደረሰበትን የውርደትና የዝቅጠት ደረጃ አሳይቷል ሲሉ በርካቶች ምስክርነታቸውን እየሰጡ እንደሚገኙ ዘጋቢያችን ከተለያዩ የማህበራዊ ድህረ ገፆች ያሳባሰባቸውን የኢትዮጵያውያን አስተያየቶች አጠናክሮ አድርሶናል።

ኢትዮጵያውያን የቪዲዮውን መለቀቅ ከተለያዩ አጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ ትንታኔ እየሰጡበት እንደሚገኙም ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በተለይ ጉዳዩ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከተከሰቱት የአየር ሐይል አብራሪዎች ከነ የጦር ሄሊኮፕተራቸው በመክዳት ወደ ኤርትራ ማምራትና የተቃዋሚ የነፃነት ሐይሎችን መቀላቀላቸው የፈጠረውን ውጥረትና ድንጋጤ ለማብረድ እንዲሁም ባህር ዳርን ጨምሮ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በአገዛዙ የተወሰዱ የግድያ እርምጃዎችንና እየተከሰቱ ያሉ ህዝባዊ ቁጣዎችንና ተቃውሞች ..... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ሕወሀት በመንግስት ስልጣን ባለቤትነትና በወንበዴነት መሐል ያለው ልዩነት ተምታቶበታል

ኢትዮጵያን በግፍና በዝርፊያ የሚገዛው የህወሀት ጉጅሌ በመንግስትነትና በወንበዴነት መሀል ያለውን ልዩነት ከ፳፫ ዓመት ስልጣን ዘመን ብኋላ እንኳን ሊገለጥለት አልቻለም። ወይም እንዳመችነቱ ሁለቱን እያምታታ መቀጠሉን እንደብልህነት ቆጥሮታል። መንግስት መሆንንና ባለህገመንግስት መባልን ከመቆነጃጃ ኩልነት ባልተናነሰ በሊጋሾቻቸው ባዕዳን ፊት ይጠቀሙበታል እንጂ ለኛ ለዜጎቹማ ወንበዴነታቸውን ሊደብቁን እንኳን አይጨነቁም።

በቅርቡ ህወሀት የትግራይ ሪፐብሊክ ለማቋቋም የክህደት ተግባሩን የጀመረበትን ፵ኛ ዓመት በዓሉን ትግራይ ውስጥ በማክበር ላይ ሳለ የቀድሞው የህወሀት ታጋይ ያሁኑ የሀገሪቱ ጦር ሎች ኤታማዦር ሹም ተብዬው ሳሞራ የኑስ የህወሀት መንግስት ያገራችን ገበሬ ወፎችን ከማሸላው ለመከላከል እንደሚጠቀምበት መስፈራሪቾ የሚጠቀምበት ሕገ መንግስት ላይ የተጠቀሰውን የሀገሪቱን ሰራዊት የፖለቲካ ገለልተኝነት ድንጋጌና ሰራዊቱ “ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ ይሆናል” የሚለውን የይስሙላ ህግ ባደባባይ አውልቆ ጥሎ ተቃዋሚዎችን የሚወነጅል ሰፊ ንግግር ሲያደርግ ተደምጧል። ሳሞራ ይህን ንግግር በሚደረግበት ቦታ አፋቸውን ከፍተው ከሚያደምጡት ውስጥ የሀገሪቱን መንግስት እንዳሻቸው የሚዘውሩት የወያኔ ሹማምንት ነበሩ። በዚህ ንግግር ውስጥ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የባዕዳን መሳሪያ ሆነው የሀገሪቱን ሉዓላዊነት እንደሚፈታተኑ ሀይሎች በመቁጠር ፍጹም ሀሰትና ጅምላ ፍረጃ ሲያደርግ “እረ ይህ ነገር በመደበኛ ስራህ የስራ ዝርዝር ውስጥ አለመኖር ብቻ ሳይሆን የተከለከለ ነው” ያለው አልነበረም። ይህን መርዝ ከተናገረና ተቃዋሚዎችም ላይ ዛቻውን ካሰማና ከወነጀለ በኋላ የህወሀት ልዩ አገልጋይነቱንም ካረጋገጠ በኋላ “ለማንኛውም እኔ ወታደር ስለሆንኩ አይመለከተኝም” ይምትል የፌዝ የግርጌ ማስታወሻ ብጤ በመናገር ህወሀት እያምታታ የሚጠቀምበትን ውንብድናና መንግስትነት አደባልቆ የሚያደርገውን ጉዞ ካላንዳች ሀፍረት አመልክቶናል። መሰረታዊ መንግስታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባለባቸው ሀገሮች የዚህ ዓይነት እነጋገር ባደባባይ አሰምቶ ለቀናት በያዙት ስልጣን ላይ መቀመጥ አይቻልም። ውንብድናና መንግስትነት ድንበር ባጣባት ኢትዮጵያ ይህ ህግ መተላለፍ ሳይሆን በገሀድ የምንኖረው የውርደት ህይወት ከሆነ አመታት ተቆጠሩ።

ግንቦት ሰባት የፍትሕ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ሀገሪቱን በቅንነት ለማገልገል ሰራዊቱን የተቀላቀለው ተራው ወታደርና የበታች ሹማምንት ይህንን መልዕክት በቅጡ ሊያደምጡት ይገባል ብሎ ያምናል። በየትኛውም ዘርፍ ያለው ሰራዊት አለቆቹ የህወሀት ስንቅ ተሸካሚዎች እንጂ የውዲቱ ሀገራችን ዘበኞችና ሉዓላዊነት አስከባሪዎች አለመሆናቸውን ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። ሰራዊቱን እያዘጋጁት ያሉትም በደል የበዛበት የገዛ ወገኑ መብቱን በሚጠይቅበትና ለመብቱ በሚታገልበት ሰዓት አፈሙዝ ወገኑ ላይ እንዲያዞር እንጂ የሀገርና የህዝብ ከለላ እንዲሆን አይደለም። ለነዚህ የወያኔ የጦር አለቆች መታዘዝ ለሀገሪቱ ዘብ መቆም ሳይሆን የህወሀት ሎሌነት መሆኑንም በቅጡ መገንዘብ ያሻል። ብዙዎች የሰራዊቱ አባላት ከዚህ ቀደም እንዳደረጉትና ዛሬም እያደረጉ እንዳሉት በተገኘው አማራጭ ሁሉ ሰራዊቱ ይህዝቡን ወገኖች እንዲቀላቀል ጥሪያችንን እናቀርባለን። በየከተሞቹ በራሳቸው በቁባቶቻቸውና በዘመዶቻቸው ስም የጦፈ ንግድ ፣ ፎቅ ግንባታና ፈንጠዝያ ላይ ያሉት የወያኔ የጦር አለቆች የቆሙት የራሳቸውን የዝርፊያ ስርዓት አደረሳቸው ድረስ ለማቆየት እንጂ ለሀገር ዘብነት አይደለም።

ሀገራችን የዜጎቿ ሁሉ መብት ተጠብቆ ስልጣኑ በህገመንግስት ተገድቦ የሚሰራ መንግስት ያስፈልጋታል ይገባታልም። በህግ አምላክ ተባብለው ህግ አክብረው መኖር ባህላቸው ላደረጉ ህዝቦች ህግና ውንብድናን አደባልቆ የሚገዛ መንግስት አይገባንም። ሰራዊቱም ለሀገር አገልግሎቱ የሚገባውን ክብር የሚያገኝበት ስርዓት እንጂ ነጋ ጠባ በወያኔ ግምገማ ከሚሸማቀቅበት በወገኖቹ ላይ እንደባዕድ እንዲተኩስ ከመታዘዝ የሚላቀቅበት ስርዓት ይገባዋል።

ከሳሞራ የእብሪትና ማናለብኝነት ንግግር የምንማረው የህወሀት የጦር አዛዦች የሀገሪቱ ወታደሮች ሳይሆኑ ህዝብ የናቁ ጭፍን ራስ ወዳድ፣ ዘረኛና ሀገር ዘራፊ ማፊያዎች መሆናቸውን ብቻ ነው። ይህን ሀቅ በተለይ በቅርብ ሆናችሁ የምትታዘቡ በተራ ውትድርናና የበታች መኮንኖች ሆናችሁ ሀገሪቱን ለማገልገል የገባችሁ የሰራዊቱ አባላት የህዝብና የሀገር ወገንተኝነታች ሁን ማረጋገጫ ጊዜው ነገ ሳይሆን ዛሬ መሆኑን ላፍታም ልትዘነጉ አይገባም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ወያኔ ለሦስተኛ ግዜ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን ለሶስተኛ ጊዜ በቴሌቪዥን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ለማርገብ አገዛዙ የቀየሰው ማዘናጊያ ወይም ማስቀየሻ ሊሆን እንደሚችል ተነግሯል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ የሚገኘው የጉጅሌው ወያኔ ከ 400 ሚሊዮን ብር በላይ የአገር ሐብት በማውደም ያዘጋጃቸው የአሶሳው የብሄር ብሄረሰቦች ቀንና የደደቢት ጉብኝትን ጨምሮ በሳለፍነው ጥቂት ቀናቶች ውስጥ የተነገረውን "የሳተላይት እናመጥቃለን" ዲስኩር በሚፈለገው መጠን የኢትዮጵያውያን ትኩረት ማስቀየስ አለመቻላቸው ተመልክቷል።

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ የነፃነት አርበኛውን የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ቪዲዮ በማሳየት አሜሪካን የሚያስንቅ የምርመራ ሥልት አለን፤ ታሳሪዎች ሳንገርፋቸው ይናዘዛሉ በማለት የድፍረቱንና የድድብናውን ልክ ሊያሳየን ሞክሯል በማለት አስተያየቱን የሰነዘረው አንድ ኢትዮጵያዊ ይህ መራር ቀልድ በአስቀያሚው የማዕከላዊ ምርመራ ሂደት ውስጥ ያለፉትንና ቶርቸርን ያስተናገዱት በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሃን ኢትዮጵያውያን ሳስብ ድፍረቱ አሳምሞኛል፤ በማዕከላዊ ቆይታቸው ጥፍራቸው የተነቀለባቸውን ወገኖቼን ሳስብ እነዚህን መርማሪዎች እና ጋዜጠኞች በፍትህ አደባባይ አገኛቸው ዘንድ ዘወትር እናፍቃለሁ ሲል ተናግሯል። አስተያየት ሰጭው ዘረኛው የህወሓት አገዛዝ ሁሌም የሚንቀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ደንቆሮ ነው ብሎ ያስባሉ። እኛስ የእነሱን ግምት በዝምታችን እያረጋገጥን እስከመቼ እንቆይ ይሆን? ሲል ጥያቄውን ለኢትዮጵያውያን በማድረስ አስተያየቱን ቋጭቷል።

በፋሺስታዊው አገዛዝ ርካሽ እና ቆሻሻ ዲስኩራቸው መካከል አንድ የናፈቁትን እና ሁሌም ባየው የማልሰለቸውን ጀግናየን አንዲን በማየቴ ፈነደኩኝ በማለት አስተያየቱን የጀመረው ሌላኛው አስተያየት ሰጭ አንተ የኛ ጀግና በአውሬዎች እጅ እንኳዋን ሆነህ አንተ የጀመርከው የነጻነት ትግል እንዴት እንቅልፍ እንደነሳቸው ባደባባይ ደግመው ሲያሳዩኝ መንፈሴን በድጋሚ አደሰው። አንተን ለመያዝ ምን ያህል ሚሊዮን ዶላሮችን እንደከፈሉ ሳስብ ግንቦት 7 የእግር እሳት ሆኖባቸው እንቅልፍ እንደነሳቸው አያለሁ። አሁን ደግሞ እራሳቸው ባመጡት መዘዝ መውጫ ቀዳዳው እንደጠፋቸው ሳይ … አንዲ ያንተ የዘወትር ድካም እና ልፋት የሆነው የነጻነት ትግል እኔም አንዳርጋቸው ነኝ ብሎ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ የደረሰበት ወቅት በመሆኑ እኮራለው! አንዳርጋቸውን ምነው ባልያዝን ብለው የሚማረሩበት ቀን፤ እኛ ደግሞ ያመረርንበት ወቅት ላይ ነንና፤ አንተን ያሰሩ እጆች የሚታሰሩበት ወቅት … አንተን ያሰቃዮ እጆች እና ደደብ ጭንቅላቶች ዋጋቸውን የሚከፍሉበት ወቅት በመምጣቱ ሁሉም ታጋዮችህ መንፈሳዊ ኩራት ተሰምቶናል። አሁንም ጽናትህ እና ጥንካሬህ የነጻነት አየር እስክትተነፍስበት ጊዜ ድረስ አብሮህ እንዲሆን ጸሎቴ ነው!! ትግላችን መራራ ድላችን ቅርብ ነው፤ ዛሬም እኔም አንዳርጋቸው ነኝ ሲሉ አስተያየት ሰጭው ቁጭታቸውን አስፍረዋል።

ቪድዮውን አይቶ ፍርድ ህዝብ እንዲስጥ ተጠይቋል። እውነቱን ለመናገር ስለምን እንዳወራ ራሱ ማውቅ እጅግ ከብዶኛል። ምንም ከማይጨበጠው ንግግር ህዝብ እንዴት የሚጨበጥ ፍርድ ሊስጥ ይችላል። ዘረኞቹ ህወሓቶች በየቀኑ አለማውቃቸውን እየነገሩን ባያቃጥሉን ጥሩ ነበር። የነሱን ዝቅጠት እንደሆነ ካውቅን ስነባበትን። ሰው እያደር እየዘቀጠ እንዴት ይሄዳል?? አሁን ጥንቅቅ ብለን ወደ ጫካ የገባን ያክል ነው የተሰማኝ በማለት በማህበራዊ ገፃቸው ላይ ሐሳባቸውን ያሰፈሩት አንድ ግለሰብ በቪዲዮው የሕወሓትን አንገት መድፋት፣ መደናበር፣ ተሥፋ መቁረጥ፤ እና የሚይዙት የሚጨብጡት ማጣታቸውን ዛሬም በድጋሚ ለህዝብ ይፋ ማድረጋችሁን መናገር ይቻላል ሲሉ አስተያየታቸውን አስፍረዋል።

አቶ አንዳርጋቸውን አፍኖ ትግሉ ይቀበራል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። የነፃነት አርማችን የሆነው አንዳርጋቸው ጽጌ በጠላቶች እጅ ውስጥ እያለ እንኳ የሚያሳየን ጥንካሬና ልበ ሙሉነት እጅግ የሚያኮራ ነው። አቶ አንዳርጋቸው አሁንም መሪያችን ነው እሱ በጠላት እጅ ቢወድቅም ሚሊዮኖች ስራውን ተረክበዋልና የተጀመረው የነጻነት ትግል ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጣበት ቀን ሩቅ አይደለም በማለት አንድ ኢትዮጵያዊ የነፃነት ትግሉን በተመለከተ ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል። አንዳርጋቸው ሁሌም ጀግናችን ነህ ምንም ነገር ብትናገር እየደረሰብህ ያለውን ስቃይና ሰቆቃ ነው የምንረዳው አይዞህ የኛ ጀግና፤ ይህ ቀን ያልፋል፤ በህይወት መኖርህን ማየታችን በቂ ነው! በማለት ለነፃነት አርበኛው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ድጋፍ የገለጹ ኢትዮጵያውያን ጥቂቶች አለመሆናቸውን ዘጋቢያችን አመልክቷል።

---

# ትናንት ከዉጭ ወራሪዎች የታደገን መከላከያ ሠራዊታችን ዛሬም ከአገር ዉስጥ ወራሪዎች ይታደገናል

አስተዋዩ የኢትዮጵያ ህዝብ እድገቱን ለሚመኙ አስተዋይ መሪዎች እለታደለምና ደሃ ነዉ፤ ረሀብተኛ ነዉ አልተማረም ወይም ኋላ ቀር ህዝብ ነዉ ማለት ይቻል ይሆናል፤ ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ ያሰኘዉን ያክል ቢደኽይ ወይም ኋላ ቀር ቢሆን ለነፃነቱ፤ ለአንድነቱና ለግዛት አንድነቱ መከበር ያለስስት ደሙን የሚያፈስ ጀግና ህዝብ ነዉ። ይህ ጀግንነት ደግሞ አንደተረት በአፍ ተነግሮ የሚያበቃ ሳይሆን በመተማ፤ በአድዋ፤ በማይጮዉ፤ በወልወል፤ በፊልቱና በጎዴ የጦር ሜዳዎች ሊወጉትና ሊወሩት የመጡ ጠላቶቹ ጭምር የመሰከሩለት የታሪክ ሐቅ ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከጀግንነቱ ጋር አርቆ አስተዋይና ታጋሽ ህዝብ ነዉ፤ ሆኖም ይህንን ህዝብ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ በተከታታይ የገዙት የገዢ መደቦች ጀግንነቱን ለራሳቸዉ ክብርና ዝና ታጋሽነቱን ደግሞ ለስልጣን ዘመናቸዉ ማራዘሚያ አድርገዉ የመከራ ዘመን እያስቆጠሩ ኖረዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ታጋሽ ህዝብ ቢሆንም እርግጫዉና ጭቆናዉ በበዛበት ቁጥር አምርሮ የሚነሳ ለገዢ መደቦች የማይመች ቁጡና እልህኸኛ ህዝብ መሆኑንም በተከታታይ አሳይቷል። ይህንን ደግሞ በ1966 ዓም ከዳር ዳር ባቀጣጠለዉ ህዝባዊ አብዮት በ1983 ዓም ደግሞ በአራቱም ማዕዘናት ባካሄደዉ ህዝባዊ አመጽ አሳይቷል። ሆኖም አብዮቱንና ህዝባዊ አመጹን ከትግል ሜዳ እስከ ፖለቲካ ስልጣን አደባባዮች ድረስ አቀነባብሮ የሚመራ የተደራጀ ህዝባዊ ኃይል ባለመኖሩ የኢትዮጵያ ህዝብ የታገለላቸዉ የትግል ዉጤቶች ሁሉ የአምባገነኖች መጠቀሚያ ሆነዉ ቀርተዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ጀግና ነዉ፤ ተጋሽ ነዉ፤ ወይም አርቆ አስተዋይ ነዉ ሲባል እንዚህ እሴቶች ወንዱን፤ ሴቱን፤ ምሁሩን፤ ገበሬዉን፤ ሰራተኛዉንና መለዮ ለባሹን ሁሉ የሚያጠቃልሉ ህዝባዊ እሴቶች ናቸዉ እንጂ የአንድ ህብረተሰብ ክፍል ልዩ ንብረቶች አይደሉም። በእርግጥም አብዛኛዉ የታሪካችን ክፍል በአገር አንድነት ግንባታና ይህንኑ አንድነት ከዉጭ ወራሪዎች በመከላከል ጦርነት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ጀግንነትን በቀጥታ የምናያይዘዉ ከዚሁ አገርንና የአገር አንድነትን ከማስከበር ስራ ጋር ነዉ። በእርግጥ አገርን ከጠላት መከላከል ጀግንነት ነዉ፤ ሆኖም መሳሪያ ተሸክሞ አገሩን ከጠላት የሚከላከል ሠራዊት ምን እለብሳለሁ፤ ምን እበላለሁ፤ በምንስ እዋጋለሁ ከሚለዉ ስጋት ተላቅቆ በሙሉ ኃይሉና አዕምሮዉ መዋጋት የሚችለዉ እንደነሱ ጀግና የሆነና በደጀንነት የተሰለፈ ህዝብ ሲኖር ብቻ ነዉ።

እስከ አድዋ ጦርነት ድረስ አገራችን ኢትዮጵያ የመሪዉን የክተት አዋጅ ጥሪ እየሰማ የሚዘምት ህዝብ እንጂ ቋሚ የመከላከያ ሠራዊት አልነበራትም። ባለፉት 60 አመታት ግን ኢትዮጵያ የምድር ጦር፤ አየር ኃይል፤ ብሔራዊ ጦርና እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ ደግሞ የባሕር ኃይልን ጭምር ያካተተ ዘመናዊ የመከላከያ ሠራዊት ነበራት። ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የአገራችንን በትረ ስልጣን እስከጨበጠበት እስከ 1983 ዓም ድረስ የነበረዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከሞላ ጎደል በመስኩ ልምድ፤ ችሎታና እዉቀት ባካበቱ ባለሙያዎች የተሞላና የአገረን ዳር ድንበር ከመጠበቅ ባሻገር ለወገናቸዉ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ደህንነት ቀና አመለካከት ባላቸዉ አገር ወዳዶች የተገነባ ሠራዊት ነበር። ወያኔ በ1983 ዓም አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ይህንን አገር ወዳድ የሆነ ፕሮፌሺናል ሠራዊት በትኖ ነዉ ለአንድ ድርጅት ጥቅምና ዝና በቆሙ፤ ፊደል ባልቆጠሩና ሙያዊ ብቃት በሌላቸዉ መሀይሞች የተሞላ መከላከያ ሠራዊት የተካዉ። እንደዚህ ስንል ግን ወያኔ በገነባዉ የአገር መከላከያ ሠራዊት ዉስጥ አገራቸዉ ኢትዮጵያን ከራሳቸዉ በላይ የሚወዱና ለአገራቸዉና ለወገናቸዉ ክብርና ጥቅም መስዋዕት ለመሆን የቆረጡ ሰዎች የሉም ማለት አይደለም፤ እንዲያዉም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሚመራዉና የግዳጅ ትዕዛዝ የሚወስደዉ አገራቸዉን በሚጠሉ ዘረኞች መሆኑ ነዉ እንጂ ዛሬም ቢሆን አብዛኛዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባል የእናት አገሩ ዳር ድንበር መደፈርና የወገኖቹ መረገጥ የሚያንገበግበዉ አገር ወዳድ ሠራዊት ነዉ።

የ1966ቱ ህዝባዊ አብዮት ሲፈነዳ የነበረዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የፊዉዳሉ መንግስት የደሞዝ ጭማሪ አድርጎለት ከህዝባዊ ኃላፊነቱ ሊያዘናጋዉ ሲሞክር - “ሎሚ ተራ ተራ፤ “ሎሚ ተራ ተራ እኛስ አግኝተናል ሲቪሉን አደራ” ብሎ የህዝብ ወዳጅነቱን ያረጋገጠ አገር ወዳድ ሠራዊት ነበር። አመጸኛዉ ደርግ ይህንን ሠራዊት ተጠቅሞ ነዉ የቀዳማዊ ኃ/ሥላሤን ስርዐት ያስወገደዉና የመሬት አዋጅን የመሳሰሉ ስር ነቀል አርምጃዊዎች መዉሰድ የጀመረዉ። አምባገነኑ ደርግ ቁልፍ በሆኑ የመከላከያ ሠራዊት ተቋሞች ዉስጥ ታማኝ የሆኑ የራሱን ሰዎች አስቀምጦ ለ17 አመታት የኢትዮጵያን ህዝብ ቢረግጥም ጄኔራል ተፈሪ በንቲን፤ ኮሎኔል አጥናፉ አባተን፤ ተስፋዬ ትርፌን፤ ጄኔራል መርዕድ ንጉሴን፤ ቁምላቸዉ ደጄኔን፤ አምሀ ደስታንና ፋንታ በላይን የመሳሰሉ እስከመጨረሻዉ ትንፋሻቸዉ ድረስ ህዝባዊ አደራቸዉን የጠበቁ ታማኝ የህዝብ አገልጋዮች በመከላከያ ሰራዊቱ ዉስጥ ነበሩ። በንጉሰ ነገስቱም ዘመን ቢሆን ገና ከጥዋቱ ከዝናና ጥቅም ይልቅ የአገራቸዉን ጥቅም ያሰቀደሙ እንደ ጄኔራል መንግስቱ ነዋይ አይነት የለዉጥ አርበኞች ነበሩ።

ወላድ በድባብ ትሂድ - ዛሬም ቢሆን እጅግ በጣም ጨለማ በሆነዉ ጨካኝና ዘረኛ ስርዐት ዉስጥ ጨለማዉን እየገለጡ በድፍረት የአገራቸዉን ህዝብ ጩኸትና ሰቀቃ አዳምጠዉ ዘረኝነት በቃ ያሉ ጀግኖች በመከላከያ ሠራዊቱ ዉስጥ አሉ። በአንድ ቋንቋና በዘር ሰንሰለት ተሳስረዉ የሚሰሩ የወያኔ ደህንነቶች መግቢያዉንና መዉጪያዉን ቆልፈዉ ለጌቶቻቸዉ ዘብ ቢቆሙም ጀግናና ጭስ መዉጪያ አያጣምና ከፍተኛ ልምድና ችሎታ ያላቸዉ የወያኔ መከላከያ ሠራዊት አባላት ከወያኔ ጎራ እየወጡ የህዝባዊ አመጹን ጎራ እየተቀላቀሉ ነዉ። ሁላችንም በየቀኑ በግልጽ እንደምናዉ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ሁለት አይነት ዜግነት ፈጥረዋል። አንደኛዉ ዜግነት ወያኔና አገራቸዉን ከድተዉ የወያኔ ተላላኪ በሆኑ እንደነ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ፤ አዲሱ ለገሰና ሬድዋን ሁሴንን በመሳሰሉ ሆድ አደሮች የተሞላ ሲሆን፤ ሁለተኛዉ ዜግነት ደግሞ አገር ወዳዶችና የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ያሉበት ነዉ። ከእንደዚህ አይነቱ በዘር ከተከፋፈለና እያንዳንዷ ኮሽ ያለች ነገር በወያኔ ደህንነት ሰራተኞች ተመዝግባ በምትመረመርበት አገር ዉስጥ ለህዝባዊ አላማ ጸንቶ መቆምና ስርዐቱን አልፈልግም ብሎ የነፃነት ኃይሎችን መቀላቀል ከፍተኛ ጀግንነትንና ቆራትነትን ይጠይቃል። ቆየት ባለዉ ግዜ እነ መቶ አለቃ ተሾመ ተንኮሉና ጄኔራል ከማል ገልቹ፤ አሁን በቅርቡ ደግሞ ሦስቱ የተዋጊ ሂሊኮፕተር አብራሪዎችና አራቱ ባለከፍተኛ ማዕረግ የአየር ኃይል ተዋጊ ጄት አብራሪዎች የወሰዱት ህዝባዊ እርምጃ ከሆነ በኋላ በሰበር ዜና ስንሰማዉ ቀላል ይመስላል እንጂ እርምጃዉ ጀግንነትን፤ ቆራጥነትንና በህይወት መወራረድን ይጠይቃል። እነዚህ ለፍትህ፤ ለነጻነትና ለእኩልነት የቆሙ ቆራጥ ዜጎች በወሰዱት እርምጃ አገር ዉስጥና ከአገሩ ዉጭ የሚኖረዉን ኢትዮጵያዊ እጅግ በጣም ደስ አሰኝቷል። በእርግጥም እነዚህ ጀግኖች የወሰዱት እርምጃ ህዝባዊ ትግሉን የሚያነቃቃና የሚያጠናክር ነዉና በልጆቻችን እርምጃ ልንኮራና ደስ ሊለን ይገባል። ሆኖም ይህ ቆራጥ እርምጃ የትግል ጥሪም ነዉና ሁላችንም ጥሪዉን አዳምጠን ዛሬ ነገ ሳንል አሁኑኑ አቤት ማለት አለብን።

ዛሬ ለአመታት በላይ ሲታመስና ሲብሰለሰል የቆየዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ብሶት ገንፍሎ ወጥቶ ወደ ለየለት ህዝባዊ አመጽነት እየተቀየረ ነዉ። ይህንን ህዝባዊ አመጽ በትክክል መርቶ ከግቡ ለማድረስና ከዚህ በፊት በተከታታይ የተፈጠሩትን የስልጣን ከፍተቶችና ስህተቶች አርሞ ትግሉን በእስማማኝ መሰረት ላይ ለማቆም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ታሪካዊና አገራዊ ሃላፊነት አለበት። በቅርቡ ተዋጊ የጦር ሂሊከፕተራቸዉን እንደያዙ የወያኔ ስርዐት በቃን ብለዉ የነጻነት ሀይሎችን የተቀላቀሉት ጀግኖች ዜና ሲሰማ ወያኔ ከፍሎ ያሰማራቸዉ ተናካሽ ዉሾቹ ያንን የለመዱትንና የተካኑበትን እንቆርጣችኋለን እንፈልጣችኋለን የሚል ተራ ዛቻቸዉን አሰምተዉናል። ከዚህ አልፈዉም ወያኔ የታጠቀዉን መሳሪያ ዘመናዊነትና ያደራጀዉን ሠራዊት ብዛት ደጋግመዉ በመጥቀስ እነሱን መንካት ከእሳት ጋር መጫወት እንደሆነ ሊነግሩን ሞክረዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ በወቅቱ ስሙን እንኳን አጣርቶ የማይጠራዉ ህወሓት ከሰሃራ በታች ተወዳዳሪ የለዉም የተባለዉ ሠራዊት የገነባ ኃይል ለምን አንደሚዋጋ እንኳን በማያዉቅ ጀሌ ጦር ማሸነፍ ከቻለ ዛሬማ ፍጹም የሆነ ህዝባዊ መሠረት ያላቸዉና ለምንና ለማን እንደሚዋጉ ጠንቅቀዉ የሚያዉቁ የነጻነት ኃይሎች ካሰቡበት ለመድረስ የሚያግዳቸዉ ምንም ምድራዊ ኃይል እንደሌለ ወያኔና ሆድ አደር ደጋፊዎቹ ተንቅቀዉ ሊያዉቁ ይገባል። ወያኔ ልቡ ስላበጠ የተለቀ ይምሰለዉ እንጁ የትልቅነቱ መገለጫ አድርጎ የሚተማመንበት የመከላከያ ሠራዊት ያቺ የፍጥጫ ቀን ስትመጣ ወያኔን ለመደምሰስ ወገኖቹን የሚቀላቀል ሠራዊት ነዉ። ባለፉት ሁለት ሳምንታት ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አባላት የወሰዱት ህዝባዊ እርምጃም በአየር ኃይሉ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ቀን፤ ግዜና ሁኔታ እየመረጠ እግረኛ ሠራዊቱም የሚወስደዉ እርምጃ እንደሆነ ያለ ጥርጥር እናምናለን።

ዉድ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ሆይ - አንተንና ወገኖችህን በዘር ከፋፍሎ እየገዛ አገርህን የሚያፈርሰዉ ወያኔ ለዚህ እኩይ ስራዉ የሚጠቀመዉ አንተኑ ከህዝብ አብራክ የወጣኸዉን የህዝብ ልጅ ነዉ። በቅርቡ ባህር ዳር ዉስጥ የቅዱስ ታቦት ማደሪያ የሆነዉን ቦታ ከቤ/ ክርሲቲያን ቀምቶ የሸቀጥ መሸጫ ለማድረግ ያደረገዉን ሙከራ የተቃወሙ ኢትዮጵያዉያን ወንድሞችህና ወንድሞችህ እንዲሁም አለም በቃኝ ያሉ መነኩሴ ጭምር በጥይት ጨፍጭፏል። በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ወልቃይት ጠገዴን ከጎንደር ቆርጦ ትግራይ ላይ የቀጠለዉ ወያኔ ይህ ፀረ ህዝብና ፀረ አገር ወንጀል አልበቃ ብሎት ለዘመናት አብሮ የኖረዉን የትግራይንና የጎንደርን ህዝብ ለማባላት ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ነዉ። በታህሳስ ወር አጋማሽ ጎንደር ዉስጥ የትግራይና ክልልና የጎንደር ሚሊሺያዎች የተኩስ ልዉዉጥ ካደረጉ በኋላ ወያኔ አገርን ለመዉረር በሚመጣ ጠላት ላይ እንጂ በራሱ ወገን ላይ መዝመት የሌለባቸዉን ከ30 በላይ ታንኮችና ከባድ መሳሪያ የታጠቁ ወታደሮች ወደ ጎንደር በማሰማራት አገሩንና ወገኑን መጠበቅ ያለበትን ሠራዊት ከገዛ ወገኖቹ ጋር እንዲፋጠጥ አድርገዋል።

በዚህ ፈታኝና እጅግ በጣም አስቸጋሪ ወቅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ሂድና ግድል በተባለ ቁጥር መጠበቅና መንከባከብ የሚገባዉን የገዛ ወገኖቹን የማይገድል አስተዋይና ወገንተኛ ሠራዊት መሆኑን በተግባር ማሳየት አለበት። አዎ! የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ምንግዜም ቢሆን በአገሩ ጠላቶችና ወራሪዎች ላይ ብቻ እንጂ እያበለና እያጠጣ .... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አየር ሐይል እየታመሰ መዉ፤ በየ ዕለቱ ተቋሙን እየከዱ የሚሰወሩ አባላት ቁጥርም እየጨመረ ነዉ

ባለፈው ረቡዕ ታህሳስ 15፣ 2007 ዓ.ም አራት የአየር ሃይል አብራሪዎች የፋሽስቱ ወያኔን በመክዳት ወደ ኬንያ ማምራታቸው መዘገቡ የሚታወስ ሲሆን ይህ ዜና ከተሰማ በኋል አንድ ተጨማሪ የአየር ሃይል ባልደረባ አገዛዙን በመክዳት ተቃዋሚዎችን መቀላለቀሉ ታውቋል። ወደ ኬንያ ያመሩት አራቱ የአየር ሐይል አባላት የሚግ 23 አብራሪ ሻምበል ገዛሃኝ ደረሰ፣ የኤም አይ 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተር አብራሪ ሻምበል ዳንኤል ግርማ፣ የኤም አይ 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተር አብራሪ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጠ፣ የኤም አይ 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተር ብሩክ አጥናኤ በአሁኑ ጊዜ በጥሩ የደህንነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ለሬዲዮ ክፍላችን የደረሰው መረጃ ያመለከተ ሲሆን ባለፉት 3 ቀናት ውስጥ የጠፋው አንድ አብራሪ በይፋ ተቃዋሚዎችን መቀላቀሉን ለማወቅ ችለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አገዛዙን በመክዳት የተቃዋሚ ሐይሎችን እየተቀላቀሉ የሚገኙት የአየር ሐይል አባላት ከዕለት ዕለት እየተበራከቱ በመምጣታቸው ሳቢያ ከፍተኛ አለመረጋጋትና ብርክ ውስጥ የገባ ሲሆን ቱባ ጉጅሌዎች አባላቱን በመለማመጥና በመለመን ተግባር መወጠራቸው ታውቋል። "ምንድነው የቸገራችሁ? ምን እናሟላላችሁ?" "እስካሁን ላጠፋነውም ይቅርታ አድርጉልን" በማለት አብራሪዎችን እየተለማመጡ እንደሚገኙ የውስጥ ምንጮች ገልጸዋል። ባለፉት 6 ወራት ብቻ 15 ልምድ ያላቸው የአየር ሃይል አባላት ስርአቱን በመክዳት በኤርትራ የመሸጉ ዲሞክራሲያዊ ሐይሎችን ተቀላቅለዋል።

በተያያዘ ዜና ከአየር ሐይሉ በተጨማሪ ከእግረኛ ተዋጊ ሰራዊቱ በየጊዜው ዘረኛውን የህወሃት አገዛዝ በመክዳት በኤርትራ የመሸጉ ዲሞክራሲያዊ ሐይሎችን የሚቀላቀሉት ቁጥር ከዕለት ዕለት እየጨመረ መሄዱ አገዛዙን ከፍተኛ አለመረጋጋት ውስጥ ከቶት እንደሚገኝ ያድረሱን ምንጮቻችን በተለያዩ የሰራዊቱ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛ ማእረግ ያላቸው መኮንኖች ተቃዋሚ ሃይሎችን ለመቀላቀል ጥያቄ እየቀረቡ እንደሚገኙና በቅርቡም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ መኮንኖች ሊከዱ አጋጣሚዎችን በማመቻቸት ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል። ጥቂት የማይባሉ መኮንኖችም የውስጥ አርበኝነትን ስራ እንዲሰሩ ተደርጎ ሰራቸውን በጥንቃቄ እያካዱ እንደሚገኙም ታውቋል።

## አንድ የአየር ሃይል አብራሪ ተቃዋሚዎችን መቀላቀሉ ተሰማ

ረቡዕ ታህሳስ 15፣ 2007 ዓም ኢሳት 4 የአየር ሃይል አብራሪዎች ወደ ኬንያ ማምራታቸውን በሰበር ዜና ካቀረበ በሁዋላ፣ አንድ ተጨማሪ የአየር ሃይል ባልደረባ ጠፍቶ ተቃዋሚዎችን መቀላለቀሉ ተሰምቷል። ባለፈው ሮብ የጠፉት የሚግ 23 አብራሪ ሻምበል ገዛሃኝ ደረሰ፣ የኤም አይ 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተር አብራሪ ሻምበል ዳንኤል ግርማ፣ የኤም አይ 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተር አብራሪ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጠ፣ የኤም አይ 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተር ብሩክ አጥናኤ በአጥሩ የደህንነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ታውቋል። “ምንድነው የቸገራችሁ? ምን እናሟላላችሁ?” “እስካሁን ላጠፋነውም ይቅርታ አድርጉልን” በማለት አብራሪዎችን እየተለማመጡ እንደሚገኙ የውስጥ ምንጮች ገልጸዋል። በአየር ሃይል ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሰራዊቱ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛ ማእረግ ያላቸው መኮንኖች ተቃዋሚ ሃይሎችን ለመቀላቀል ጥያቄ እየቀረቡ ቢሆንም፣ ከተቃዋሚዎች በኩል ” ውስጥ ሆናችሁ ታገሉ” የሚል መልስ እየተሰጠ ነው። አንድ ስማቸው እንዳይነገር የፈለጉ የተቃዋሚ አመራር እንደተናገሩት የሃይል ትግሉን ለመቀላቀል የሚጠይቁ ከፍተኛ መኮንኖች ትግላቸውን በውስጥ ሆነው እንዲያካሂዱ ተነግሯቸዋል።

መንግስት አራት አብራሪዎች አልጠፉም ሲል ማስተባባያ መስጠቱ በድሬዳዋና ሌሎች ምድቦች ያሉ የአየር ሃይል አባላትን በእጅጉ እንዳስገረመ ምንጮች አክለው ገልጸዋል። የአየር ሃይል አባላት ስርአቱን አናገለግልም በማለት በብዛት መጥፋታቸው የህዝብ ትኩረት ስቦ በሚገኝበት ወቅት፣ መንግስት ትኩረቱን ለማስቀየር በሚመስል መልኩ በግፍ እስር ላይ የሚገኘውን የግንቦት7 ዋና ጸሀፊ አንዳርጋቸው ጽጌን በኢቲቪ አቅርቦ አሳይቷል። ኢቲቪ ያቀረበው ፊልም የተቆራረጠና መልክቱ በግልጽ የማይሰማና አላማው የማይታወቅ መሆኑ፣ በማህበራዊ ድረገጾች ሌላ የመነጋገሪያ አጀንዳ ፈጥሯል። ባለፉት 6 ወራት ብቻ 15 ልምድ የነበራቸው የአየር ሃይል አባላት ስርአቱን በመተው ተቃዋሚዎችን ተቀላቅለዋል። የአየር ሃይል አዛዦችን ለማግኘት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም።

## በሰሜን ኢትዮጵያ ዉጥረት ዉስጥ ነዉ፤ በአካባቢው ከፍተኛ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ይታያል

በመላው ኢትዮጵያ ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃውሞንና እምቢተኝነትን እያስተናገደ የሚገኘውና በአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫዎች እየተቀሰቀሱ የሚገኙትን ህዝባዊ ተቃውሞና እምቢተኝነቶችን በሐይል በማፈን በትረ ስልጣኑን ለማርዘም እየሰራ የሚገኘው አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከሰሞኑ ከወደ ሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ በባህር ዳር፤ ጎንደር፤ ደብረማርቆስና ሌሎችም አጎራባች ከተሞች እየተቀሰቀሱ ያሉትን ህዝባዊ ተቃውሞችንና እምቢተኝነቶችን ተከትሎ የነገሰውን ውጥረት ለማፈን ከፍተኛ ወታደሮችንና የጦር መሳሪዎችን ወደ አካባቢው እያንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ለማወቅ ችለናል። በአካባቢዎቹ የተቀሰቀሱት ህዝባዊ ቁጣና የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች አሁንም ድረስ መኖራቸውን ያደረሰን የውስጥ ምንጫችን የተቃውሞ እንቅስቃሴዎቹ ወደ ግጭት ሊያመሩ እንደሚችሉ ተመልክቷል። ከሰሞኑ የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በደብረ ማርቆስ፤ ጎንደርና ወሎ አካባቢዎች ለተማሪዎችና ለመምህራን አስገዳጅ የፖለቲካ ስልጠና የሰጠ ቢሆንም በሁሉም ቦታዎች ከፍተኛ ተቃውሞችን ከማስተናገዱም በላይ በአንዳንድ ቦታዎችም ስብሰባዎች ያለ ምንም ስምምነት መበተናቸው ተዘግቧል። በአንዳንድ ከተሞች በተማሪዎቹ የተቀጣጠለውን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማፈን አገዛዙ የሐይል እርምጃ መውሰዱ አይዘነጋም።

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በጎንደር፤ በደብረማርቆስና በወሎ እንዲሁም በሌሎቹም አጎራባች ዞኖችና ወረዳዎች ላይ እየተቀጣጠሉ የሚገኙትን ህዝባዊ ተቃውሞዎችንና እምቢተኝነቶችን ለማፈን ህብረተሰቡን በማስፈራራትና በማፈን እኩይ ስራው መጠመዱን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በቅርቡ በባህር ዳር በተቀሰቀሰው ተቃውሞ ከ 6 በላይ ንፁሃን ዜጎች በአገዛዙ ቅጥረኛ ፌደራሎች በአሰቃቂ ሁኔታ በጥይት ተደብድበው መገደላቸውንና ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ሰዎች በግፍ ታስረው አሁን ድረስ ከፍተኛ ማሰቃየት እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝ መዘገቡ ይታወሳል።

## ለተወሰኑ ጊዜያት ረገብ ብሎ የነበረው የህዝበ ሙስሊሙ ትግል ዳግም በተጠናከረ ሁኔታ አገርሽቶ ቀጥሏል

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ላለፉት 3 አመታት የእምነት ነፃነታቸውን ለማስከበር በመንቀሳቀስ ላይ በሚገኙት ንጹሐን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችንና በድሎችን ማለትም ግድያ፤ የጅምላ እስርና፤ ድብደባ እየፈጸመባቸው መኋዙ የሚታወቅ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የትግል ስልቶቻቸውን ለመፈተሽና ለመቀየር በሚል ለወራቶች ረገብ ብሎ የነበረው ፍጹም ሰላማዊው የህዝበ ሙስሊሙ ትግል ዳግም ማገርሸቱን ለማወቅ ተችሏል። በዚህ በያዝነው ሳምንት መጀመሪያ ላይ በአዲስ አበባ ወሎ ሰፈር የሚገኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በግድግዳ ላይ ጽሁፎችና መፈክር በተጻፈባቸው ወረቀቶች አሸብርቀው ማደራቸውን ያደረሰን የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን የተጻፉት መፈክሮች ህዝበ-ሙስሊሙ መብቱን ለማስከበር ያነሳቸውን ጥያቄዎች የሚያሰተጋቡና መብታቸውን በመጠየቃቸው ብቻ በአገዛዙ የፈጠራ ወንጀል ተከሰው ለእስር የተዳረጉት የሙስሊም መሪዎች እንዲፈቱ የሚጠይቁ መሆናቸውን ለማወቅ ችለናል። ከተለጠፉት መፈክሮች መካከል ‘’አሸባሪዎች አይደለንም፣ አሸባሪው ወያኔ ነው፤ የታሰሩት ሙስሊሞች በአስቸኳይ ይፈቱ! ኮሚቴው ይፈታ! የሂጃብ ገፈፋው ይቁም! ትግሉ ይቀጥላል! እና ፍትህ ናፈቀን!” የሚሉት ይገኙበታል። በግድግዳ ላይ ከተጻፉትና ከተለጠፉት ባሻገር ሙስሊሞች መብታቸውን ለማስከበር ያነሷቸውን ጥያቄዎች የሚያስተጋቡ በርካታ ወረቀቶችም መበተናቸው የታወቀ ሲሆን እያደረጉት ባለው ፍጹም ሰላማዊ ትግል የማንኛውም አይነት እምነት ተከታይ ወገኖቻቸው ነግ በኔ በማለት ከጎናቸው በመሰለፍ አጋርነታቸውን ያሳዩዋቸው ዘንድ ወገናዊ ጥሪያቸውን ዳግም እንዳቀረቡም ለማወቅ ችለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ የህዝበ ሙስሊሙን ፍጹም ሰላማዊ ትግል ለማደናቀፍና ለማፈን የተለያዩ የሐይል እርምጃዎችን እየወሰደ ቢሆንም ማስቆም አለመቻሉ የሚታወቅ ሲሆን በተለይ አገዛዙ ህዝበ ሙስሊሙን ጨምሮ የመላ ኢትዮጵያውያንን የነፃነት ጥያቄዎችንና እንቅስቃሴዎችን ለማፈን የዘረጋው የ1 ለ 5 ጥርነፋ ወጤት ሊያስገኝለት አለመቻሉ ቱባ ጉጅሌዎችን ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ከቷቸው እንደሚገኝ የውስጥ ምንጮቻችንን ዋቢ በማድረግ መዘገባችን ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## በድሬዳዋ አየር ሃይል ውጥረት የበዛበት ግምገማ ተካሄደ

አራት ከፍተኛ ማእረግ ያላቸው የአየር ሃይል አብራሪዎች መጥፋታቸውን ተከትሎ በድሬዳዋ የአየር ሃይል ምድብ ሲካሄድ የነበረው የ3 ቀናት ግምገማ ሃሙስ እለት ተጠናቋል።በግምገማው ላይ አብራሪዎች፣ አሰልጣኞች፣ ቴክኒሻኖችና ሰራተኞች የተገኙ ሲሆን፣ ሰራተኞቹ ስለጠፉት አብሪዎች የተሰማቸውን ስሜት እንዲናገሩ፣ የሚያውቁትን ሚስጢር እንዲያወጡ ሲገደዱ ሰንብተዋል። ብዙዎች" ስለጠፉት አብራሪዎች ምን ትላላለችሁ?' እየተባሉ ሃሳባቸውን እንዲናገሩ የተጠየቁ ሲሆን፣ በሚሰጡት ሃሳብ ተንተርሶ የደህንነት ሃይሎች ተጨማሪ ምርምራ እንደሚያካሂዱ በግምገማው ላይ የተሳተፉ ወገኖች ገልጸዋል። በግመገማው ላይ የተገኙት አዛዦች በሙሉ እጅግ ተናደው መሰንበታቸውን የሚናገሩት ምንጮች፣ በግቢው ውስጥ ያለው ድባብ ውጥረት የበዛበት በመሆኑ ሰራተኞች ተረጋግተው ስራቸውን ለመስራት አልቻሉም። የእርስ በርስ ጥርጣሬውና አለመተማመኑ የከፋ ደረጃ ላይ መድረሱንም ሰራተኞች ገልጸዋል። በዚህ ሳምንት ስርአቱን አናገለግልም ብለው ወደ ኬንያ የተሰደዱትን አብራሪዎች በተመለከተ ኢሳት ለወደፊቱ ዝርዝር መረጃዎችን እንደሚያቀርብ ለመግለጽ ይወዳል።

## አሜሪካ በየቀኑ እየቀጠቀጠን ነዉ፤ ቪኦኤን ድምጥማጡን ማጥፊት አለብን

ባለፈዉ አመት የሚመራዉን የአማራ ህዝብ ሙልጭ አድርጎ የተሳደበዉ የብአዴኑ ዋና ጸሃፊ አለምነው መኮንን አሜሪካ በየቀኑ እየቀጠቀጠን ስለሆነ ቢቻል ቪኦኤን ድምጥማጡን ማጥፊት ነበረብን ሲል መዛቱን ዘጋቢዎቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። አለምነው መኮንን ይህን የተናገረዉ መጪውን ምርጫ አስመልክቶ ለተመረጡ የብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ አባላትና ለባለድርሻ አካላት ባደረገዉ ገለጻ ነው።

አቶ አለምነው ነጻ ሚዲያ በሌለበት አገር ኢሳትና ቪኦኤን የመሳሰሉ ነጻ ሚዲያዎችን ማፈን ተገቢ ነወይ የሚል የጽሁፍ ጥያቄ የቀረበላቸው ሲሆን፣ ቪኦኤ በአሜሪካ መንግስት ሳንባ የሚተነፍስ ነው ፣ የአሜሪካ መንግስት አላማ ደግሞ የሊበራሊዝም አላማ ነው በዚህም የነተሳ የኢትዮጵያን መንግስት ሌት ከቀን እየቀጠቀጠው ነው ብለዋል። የውጭ ባለሃብቶች መጥተው የኢትዮጵያን ባንክ መምጠጥ ይፈልጋሉ ያሉት አቶ አለምነው፣ ቴሌም በውጭ ቱጃሮች እንዲያዝ ይፈልጋሉ ሲሉ አብራርተዋል። ቴሌ ማለት ገንዘብ የሚያመርት ማሽን ነው የሚሉት አቶ አለምነው፣ ደርጅቱ በየአመቱ 6 ቢሊዮን ብር ለአባይ ግድብ ድጋፍ እንደሚያደርግና የአባይ ግድብም በቴሌ ትርፍ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል። ታዲያ ይህን ነው አሜሪካኖች ሊቀሙን የሚፍለጉት ሲሉ ለተሰብሳቢው አስረድተዋል። እነዚህ ሚዲያዎች ቢችሉ ምድር እንዲገለባብጥ ፣ አገሪቱ የተኩስ አገር እንድትሆን ይፈልጋሉ ያሉት አቶ አለምነው ፣ አቅም ስለሌለ ነው እንጅ አቅም ቢፈቅድማ ድምጥማጣታቸውን ማጠፋት ነበር ብለዋል።

## አቶ መለስን የሸለመው"ያራ" ኩባንያ" ከባድ የሙስና ክስ ተመሰረተበት

በምርጫ 97 ወቅት ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን የሸለመው "ያራ" የተሰኘ የኖርዌይ ድርጅት በሙስና ተከሰሰ ፤ ኢትዮጲያውያንም ተጨማሪ ክስ ያቀርባሉ። በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1997 ዓመተ ምህረት ለቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ 200 000 ዶላር የሸለመውና- ሽልማቱን ተከትሎ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ የኢትዮጵያ ብቸኛ የማዳበሪያ አቅራቢ የሆነው የ"ያራ ኩባንያ"ዳይሬክተር ቶርሊፍ ኢንገር፤ በኖርዌይ ታሪክ ትልቅ በተባለው የሙስና ክስ ነገ ጠዋት ኦስሎ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ። የያራ ዳይሬክተር የተከሰሱት፤ በህንድ እና ሊቢያ ከማዳበሪያ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሙስና እንደሆነ ተመልክቷል።"ያራ ኩባንያ" በእነዚህ ሁለት ሃገራት ውስጥ ባልተገባ መልኩ ጨረታ አሸንፎ ማዳበሪያ የማቅረብ ኮንትራት ያገኘው፡- ዳይረክተሩ ከጨረታው በፊት ለሁለቱ ሃገራት ባለሥልጣኖች 8 ሚሊዮን ዶላር በመስጠታቸው መሆኑን የኖርዌይ የዜና አገልግሎት (NRK) ዘግቧል።

እንደ ኤን. አር ኬ ዘገባ፣ የ71 አመቱ ቱርላይፍ ኤንገን ጥፋተኛ ሆነው ከተገ፤ የቀረውን ህይወታቸውን በእስር ቤት ያሳልፋሉ። በሰኔ ወር 1997 ዓመተ ምህረት በኢትዮጳያ ታጣቂዎች ከምርጫው ጋር ተያይዞ ተቃውሞ ያሰሙ ንጹሀንን በገደሉ ማግስት የአሁኑ ተከሳሽ የያራ ኩባንያ ዳይሬክተር- "የምግብ ምርትን በመጨመርና ድህነትን በመቀነስ ላደረጉት አስተዋጽኦ በሚል" ለአቶ መለስ ዜናዊ የ 200 ሺህ ዶላር ሽልማት ማበርከታቸው ይታወሳል። "ያራ" ለአቶ መለስ ሽልማቱን ባበረከተ በጥቂት ወራት ውስጥ በኢትዮጵያ ማዳበሪያ ለማቅረብ የወጣውን ጨረታ እንዲያሸንፍ የተደረገ ሲሆን፤ በጨረታው ስምምነት፡- ከገቢው 30 በመቶው "ኢፈርት" ተብሎ ለሚጠራው የህወሀት ካምፓኒ የሚተላለፍ ሆኖ ቆይቷል። ይህ ከሆነ ከሰባት ዓመታት በሁዋላ ነው "ያራ" በሊቢያና በህንድ ከማዳበሪያ አቅርቦት ጋር በተያያዘ በ8 ሚሊዮን ዶላር ሙስና ክስ የተመሰረተበት።ይህን ክስም ተከትሎ በምእራብ ኖርዌይ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጲያውያን "ያራ" በኢትዮጲያ ማዳበሪያ አቅራቢ ለመሆን ያሸነፈበት መንገድ በኖርዌይ አቃቤ ህግ እንዲመረመርና እንዲጣራ ተጨማሪ ክስ ለማቅረብ ተዘጋጅተዋል።

## ሁላችንም አንዳርጋቸው ጽጌን እንሁን!!! ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

የፊልሙ ማጀቢያዎች የነበሩት የሂውማን ራይትስ ዎች ሪፓርት፣ ስለእንግሊዝ ጋዜጣ የተነገረው፣ አሜሪካ ስለምትፈጽመው የሰብዓዊ መብት ጥሰት የተዘከረው፣ ወዘተ ... ወዘተ የሚያመላክቱት አንድ አቢይ ሀቅ አለ። ይህም ኢትዮጵያዊያን ፀሐይና ብርድ ሳይበግራቸው "እኔ አንዳርጋቸው ጽጌ ነኝ" እያሉ በእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት፣ በእንግሊዝ ኤምባሲዎች እና በአውሮፓ ኅብረት ሲያደርጓቸው የቆዩ ተቃውሞዎች ውጤታማ መሆናቸው ነው። በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የፈጠሩት ጫና ወያኔን ወደ ተከላካይነት አውርዶት "እኔ ንፁህ፣ አሜሪካ ርኩስ" እንዲል አድርጎታል። ወያኔ፣ ስለንፅህና ምስክርነት ይሰጥልኛል ብሎ ተስፋ ያደረገው ደግሞ ራሱ ነፃነቱን ገፎ እስረኛው ያደረገው ሰው መሆኑ ጥረቱ እንደምን ውል አልባ እንደሆነበት ያሳያል። ንፅህናን ነፃ ባልሆነ ሰው ማስመስከር ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው? ይህ ክስተት፣ የኢትዮጵያዊያን ዘርፈ ብዙ ተቃውሞ የወያኔን የመከላከል አቅም ማዳከሙን በግልጽ ያሳያል። ይህ ለኢትዮጵያዊያን ትልቅ ብሥራት ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት ምክንያቶች ህወሓት አንዳርጋቸውን ወደሚዲያ ለማቅረብ ምክንያት ይሁኑ እንጂ የአንዳርጋቸው ለሶስተኛ ጊዜ በወያኔ ቴሌቪዥን መታየት በኢትዮጵያዊያን ላይ የፈጠረው ስሜት ህወሓት ከጠበቀው ፈጽሞ የተለየ ነው።

ኢትዮጵያዊያን አንዳርጋቸውን ሲያዩ የሚታያቸው ጽናት፣ አርበኝነትና አልበገር ባይነት ነው። የአንዳርጋቸው ምስል በታየ ቁጥር ኢትዮጵያዊያን ፀጉራቸው ይቆማል፤ ደማቸው ይፈላል። ወያኔዎች አንዳርጋቸውን የፈለጉትን ቢያናግሩት ችግር የለም። ለጊዜው በእጃቸው ውስጥ ስለሆነ ያላለውን ያለ ሊያስመስሉ እንደሚችሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል። ወደፊት ደግሞ ሊናገር ያልፈለገውን ያናግሩት ይሆናል። ይህ ሁሉ የሚያመጣው ለውጥ የለም። አንዳርጋቸው ስለወያኔ ምንነትና ማንነት ማንም ሳያስገድደዉ በነፃነት አገር ዉስጥ በግልጽ ተናግሯል፣ አሁንም ወያኔዎች እራሳቸዉ በሰሩት ፊልም ዉስጥ እነሱ በማይገባቸው መንገድ ለኢትዮጵያን ሕዝብ ተናግሯል። እንኳንስ እነሱ እሱም ራሱ በማይገባው መንገድ አንዳርጋቸው ኢትዮጵያዊያን ልብ ውስጥ ገብቷል። አንዳርጋቸውን ስናይ በህወሓት ፋሽስታዊ መዳፍ ውስጥ የወደቁብንን ጀግኖቻችንን ሁሉ ያስታውሰናል። በአስር ሺዎች ይቆጠራሉ። የአንዳርጋቸው ምስል ለግላጋ ወጣቶች፣ በሳል አዛውንት፣ ምርጥ ወንድሞችና እህቶች በወያኔ እስር ቤቶች ፍዳቸውን እያዩ መሆኑን ያስታውሰናል። ምስሉ ብቻውን ያናግረናል፣ ያነቃናል፣ ያነሳሳናል!!!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አንዳርጋቸው ጽጌን፣ በርካታ ጀግኖቻችንን፣እራሳችንንና አገራችንን ከወያኔ እስር ነፃ ለማውጣት ክንዳችንን እናበርታ፤ ሁላችንም "እኔም አንዳርጋቸው ጽጌ ነን" እንበል፤ ሁላችንም አንዳርጋቸው ጽጌን እንሁን ይላል። **ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ኢትዮጵያዊያን አንዳርጋቸውን ሲያዩ የሚታያቸው ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

የፊልሙ ማጀቢያዎች የነበሩት የሂውማን ራይትስ ዎች ሪፓርት፣ ስለእንግሊዝ ጋዜጣ የተነገረው፣ አሜሪካ ስለምትፈጽመው የሰብዓዊ መብት ጥሰት የተዘከረው ሁሉ የሚያመላክቱት አንድ አቢይ ሀቅ አለ።"ያለው ንቅናቄው፤ ይህም ኢትዮጵያዊያን ፀሐይና ብርድ ሳይበግራቸው "እኔ አንዳርጋቸው ጽጌ ነኝ" እያሉ በእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት፣ በእንግሊዝ ኤምባሲዎች እና በአውሮፓ ኅብረት ሲያደርጓቸው የቆዩ ተቃውሞዎች ውጤታማ መሆናቸውን ነው ብሏል። "ኢትዮጵያዊያን አንዳርጋቸውን ሲያዩ የሚታያቸው ጽናት፣ አርበኝነትና አልበገር ባይነት ነው። የአንዳርጋቸው ምስል በታየ ቁጥር ኢትዮጵያዊያን ፀጉራቸው ይቆማል፤ ደማቸው ይፈላል።" ያለው ግንቦት 7፤ ወያኔዎች አንዳርጋቸውን ወደፊትም እንዲሁ ሊናገር ያልፈለገውን ቢያናግሩት የሚፈጠር ምንም ለውጥ እንደሌለ አስምሮበታል።

"እንኳንስ እነሱ አሳሪዎቹ እሱም ራሱ በማይገባው መንገድ አንዳርጋቸው ኢትዮጵያዊያን ልብ ውስጥ ገብቷል።" ያለው ግንቦት 7፤" አንዳርጋቸውን ስናይ በህወሓት ፋሽስታዊ መዳፍ ውስጥ የወደቁብንን በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ጀግኖቻችንን ሁሉ ያስታውሰናል። ያነቃናል፣ ያነሳሳናል!!!" ብሏል። ንቅናቄው በመጨረሻም "አንዳርጋቸው ጽጌን፣ በርካታ ጀግኖቻችንን፣ እራሳችንንና አገራችንን ከወያኔ እስር ነፃ ለማውጣት ክንዳችንን እናበርታ፤ ሁላችንም "እኔም አንዳርጋቸው ጽጌ ነን" እንበል፤ ሁላችንም አንዳርጋቸው ጽጌን እንሁን "ሲል ለ ኢት ጾያ ህዝብ ጥሪ አቅርቧል።

## ትናንት ከዉጭ ወራሪዎች የታደገን ... ( ከገጽ 3 የዞረ )

ባሳደገዉና እኔንና አገሬን ጠብቅ ብሎ ባስታጠቀዉ ህዝብ ላይ በምንም አይነት አፈሙዙን አያዞርም። ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ህዝብ ከወያኔ በላይ ጠላት የላቸዉም። ህዝብና አገር እስከ ምድር ፍጻሜ ድረስ አብረዉ የሚዘልቁ ተከታታይ ክስተቶች ናቸዉ፤ ወያኔ ግን ትናንት በጠመንጃ ሀይል መጥቶብን እኛንና አገራችንን ለማጥፋት የሚታገል የለየለት ጠላት ነዉ። ከዛሬ ጀምሮ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ባገኘዉ አጋጣሚ ሁሉ ወያኔን ከዉስጥ ሆኖ መቦርቦር አለበት፡ ይህንን ማድርግ ካልቻለ ደግሞ ወያኔ ከወገኖቹ ጋር እንዲዋጋ ሲያስማራዉ ወያኔን እየከዳ ከነጻነት ኃይሎች ጋር ተቀላቅሎ ወያኔን ለመደምሰስ በሚደረገዉ ትግል ዉስጥ ወሳኙን ሚና መጫወት ይኖርበታል። ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከዚህ ቀደም እንዳደረገዉ ሁሉ አሁንም እንደገና ለኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት . . . ና ተቀላቀለንና አንድ ላይ ሆነን ወያኔንና ወያኔ የገነባዉን ዘረኛ ስርዐት ቀብረን የኢትዮጵያን ህዝብ ከዉርደት፤ ከእስር፤ ከድብደባ ከግድያና ከስደት እናድን የሚል አገራዊ ጥሪዉን ከአደራ ጋር ያስተላልፋል።